# ንስሩ ዶሮ እንዳይሆን...

*አጩሌ ከአሜሪካ ግቢ 03-29-18*

ስለ መጪው ጊዜ ስንተነብይ፣ ወይም Predict ስናደርግ ነባራዊ ሁኔታውን ተንትነን፣ ራሳችንን መጪውን ጊዜ በሚያስከትለው የጊዜ ቀመር ውስጥ አስገብተን፣ አለያም እንደ ታዛቢ ቆመን ከሆነ ያሰብነውና ይሆናል ያልነው መሆኑ አይቀሬ ሊሆን ይችላል። በዚህ የመነሻ ሃሳብ ራስን ማስገባትና ታዛቢ ሆኖ መቆም ሲባል፣ በተተነበየው አሉታዊ ጉዳይ መሳካት ላይ ያለ ልዩነት ለመጪው ጊዜ ትንበያ አስተዋፅኦ ማድረግ ማለት ነው። ይህም ሲባል በመቆምና በመሳተፍ የተተነበየውን ጉዳይ መዳረሻ ለማየት መቋመጥ ማለት ነው። ይህ የትንበያ ተሳትፎ ለአሉታዊው ውጤት ድርሻን መወጣት ወይም ማበርከት ማለት ነው።

ኢህአዴግ፣ የኢህአዴግን ሊቀመንበር ከመምረጡ አስቀድሞ በነበሩት ረጅም የውይይት ጊዜያትም ሆነ ከዚያ በፊት የብዙዎች ትንበያ አብቅቶልናል፤ ወይም ሊያበቃልን ነው በሚል የሃሳብ አዙሪት ውስጥ ሲሽከረከር የቆየ ነው። ለዚህ አሉታዊ ትንበያ ስኬት ቆመውም፣ ተሳትፈውም አስተዋፅኦ ያደረጉ የነበሩትን ያህል ከትንበያው ማዶ ሲታይ የነበረውን ጭላንጭል አስቀድሞ ተመልክቶ፣ ጭላንጭሉን ወደ ሰፊ ብርሃን ከመቀየር በፊት ሌሎችም የሩቁን ጭላንጭል እንዲያዩት የሚያስችል መስመር ነበረ።

ይሄ ጭላንጭል እንዳለና እንደነበረ ብዙዎች ያለማመንታትና ያለ ጥርጣሬ የተቀበሉ፣ ያመኑ ወይም አለ ብለው ሲመሰክሩና ሌሎችም እንዲቀበሉና እንዲያምኑ ሲያደርጉ የቆዩ ቢሆንም፣ ጭላንጭሉ በእርግጥ እንዳለ ተረድተው፣ መርምረውና አረጋግጠው ሲደሰኩሩ ባለመክረማቸው፣ ሌላው ጎርፍና ንፋስ ከወዲህ ወዲያ ሲያላጋቸው ቆይቷል። ኢህአዴግም ይህን ያልተረዳ ሃይል ለማስረዳት፣ ለማሳየትና ለማሳመን ቀይ መስመሩን ጭምር አልፎ ረጅም ርቀት በመጓዝ ከባድ ዋጋ ከፍሏል።

እንዲያውም የከፈለው ዋጋ የቀነሰለት በቀዳዳው ውስጥ ሲታይ የነበረውን ብርሃን ሊያዳፍኑት የተዘጋጁ ሀይሎች አሉ የሚለውን ከጥርጣሬ የዘለለ ተጨባጭ እውነታ የአገራችን ህዝብ ወደመጨረሻው ላይ በግልፅ ስለተረዳው ነው። በሌላ አነጋገር በጭላንጭል በሚታየው ብርሃን ወገግታ እያገኘ የመጣው ህዝብ ያለ ማመንታት ጨለማውን የሚያፋጥኑትን የውስጥም፣ የውጭም ሀይሎች እጅ አላስገባ ብሎ ስለተከላከለ ነው።

አሁን ለኢህአዴግ የሚያስፈልገውና የሚያሻው ራሱ በተግባርና በምግባር ሳያምን መስመሩን የሚሰብክለት አይደለም። ሲዳምን እየዳመነ፣ ሲፈካ የሚፈካ የመስከረም አበባ ለኢህአዴግ አያሻውም። እንዲያውም ኢህአዴግ አሁን ለገጠመው ፈተና ገለታ ይግባውና ፈተናውን ለማለፍ የሄደበት መንገድና እያንዳንዱ ውሳኔ ህዝባዊ መሆኑን አረጋግጦለታል። ህዝቡን እያዳመጠና ህዝቡ እንዲያዳምጠው እያደረገ በሰከነ ሁኔታ የወሰዳቸው እያንዳንዱ ታክቲካል ርምጃ ይህቺ አገር አበቃላት ብለው የተነበዩትንና ለትንበያው መሳካት ቆመውና ተሳትፈው አስተዋፅኦ ያደረጉትን ጭምር በሚያስገርም ሁኔታ አቸንፎታል።

ኢህአዴግ ይህን ማድረግ ያስቻለውን ጉልበትና ጥበብ እንፈትሽ።...

ከነገረ ቀደም፣ ይህቺ አገር አበቃላት የሚለው ሀሳብ ተራ ሟርት አልነበረም። በእርግጥም የጥፋት ዳርቻችን የት ድረስ እንደሆነ በደንብ መመልከት የምንችልበት መነፅር ነበረን። ከሩቅ በምሳሌ ሳናጣቅስ አገራችን ውስጥ ሲፈፀሙ የነበሩ ጥፋቶችና የጥፋቶቹ ሀሳብ መነሻዎች አስደንጋጭ ነበሩ። ስለዚህም ይህን ተመልክቶ አበቃልን ብሎ መተንበይ በጣም ቀላሉ ትንታኔ ነበረ። በሌላ አነጋገር ትንታኔው ትክክል ነበረ። በዚህ ትንታኔ ውስጥ ሆነው የተለያየ መላምት ሲሰጡ የነበሩ ወገኖችም ከመዳረሻ አኳያ ትክክል ስለነበሩ በተለያዩ ወገኖች ተደማጭ ነበሩ። እነዚህ ወገኖች መዳረሻው ላይ የጠበቁት ስላልሆነ ተሳስተዋል ማለትም አይደለም። በሂደቱና በሚታያቸው ልክ ትክክል ነበሩና።

ይህ ያበቃልን ትንታኔ ኢህአዴግም ውስጥ አልነበረም ማለት አይቻልም ብቻ ሳይሆን አበቃልን የሚለው ስሜት በተጨባጭ ነበረ። በኢህአዴግ መስመር ውስጥ ግን ፈፅሞ አልነበረም። ፈተናን ማቸነፍ አዲሱ ያልሆነው ኢህአዴግ ታላቁ ብርታት መስመሩ ነውና፣ የሚያጋጥመውን እያንዳንዱን ፈተና ከመስመሩና ከአገራዊና ዓለማዊ ሁኔታው ጋር እያመሳከረ መፍትሄ እንደሚያበጅ የማይጠራጠሩም ነበሩ። ብዙዎች ግራ መጋባታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ።

ኢህአዴግ እነዚህ ሁሉ ፈተናዎች ገጥመውት ሳለ በዚያ አዙሪት ውስጥ አለመግባቱ ንስርነቱን አስጠብቆ ለመጓዝ ረድቶታል። እዚያው ኢህአዴግ ውስጥ ያሉ ንስሮች በህዝበኝነት ተይዘው ላባቸውን ሲነጩአቸውና እንደ ዶሮ ሊያኖሯቸው ትግል ሲያደርጉ ከነበሩ ሀይሎች በማላቀቅ ኢህአዴግነት ንስርነት መሆኑን እንዲቀበሉ በረጅም የግምገማ መድረኩ አሳምኗቸዋል። የንስርና የዶሮ አኗኗር የተለያየ መሆኑንም አሳይቷቸዋል።

ኢህአዴግ አዙሪቱን ለማስቆም ከጭላንጭሉ ወዲያ ማዶ ማየቱ በእጅጉ ጠቅሞታል። ታላቁ መሪ ጓድ መለስ ዜናዊ ይለው እንደነበረው “አንድ እጁን ታስሮ የነበረው ኢህአዴግ” ሁለት እጁን በመያዙ፣ ቀዩን መስመር ጭምር አልፎ በወሰደው ታክቲካል እርምጃ እጁንም አስለቅቋል፣ ወደ መስመሩም ተመልሷል። ይባስ ብሎ ህዝባዊነቱን አጠናክሮ መውጣት የሚያስችለውን ታላቅ እድልና አጋጣሚ ተጎናፅፏል።

ይህን እውነታ በተጨባጭ ማረጋገጥ የቻለው ኢህአዴግ በነባራዊ የሁኔታ አዝማሚያና ትንበያ በሚታየው ሀቅ ላይ ሳይመሰረት፣ ሀቁን አልፎ በሚተገበረው መፍትሄ ዙሪያ ጊዜ ሰጥቶና ንስር ሆኖ በማየቱ፣ አይቶም ተራማጅና እልፍ ያለ እርምጃ በመውሰዱ ሁለት እጆቹን አስለቅቋል። ሌላ ብዙና ብዙሚሊዮን እጆችንም የራሱ ማድረግ ችሏል። እንዲህ ላለው ውጤት እንዲበቃ ያደረገውም በደረሰው ተከታታይ ጥፋት ከሚጠበቀው አሉታዊ ውጤት ይልቅ፣ በአሉታዊ ውጤት ሊሸፈን በማይችለው፣ ህዝቡም ራሱ ሲሳተፍበት በነበረው ብርሃናማ ጉዞ ፈተናው ሊደፈቅ እንደሚችል አምኖ ለስኬቱ በመስራቱ ነው።

የፌስቡኩ መስራች ማርክ ዙከርበርግ፣ አንድ ወዳጄ የተናገረውና የምወደው ጥቅስ ብሎ ከገለፀው “Optimists tend to be successful & Pessimists tend to be right” ከሚለው ሃሳብ ልዋስና፣ ኢህአዴግ ፀለምተኛ ባለመሆኑ በዚህች አገር ሊፈጠር ከነበረው ትክክለኛ አሉታዊ ትንበያ ህዝብና አገር እንዲያመልጡ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

ይህም ሆኖ ኢህአዴግና ህዝቡ አሸንፈዋል ማለት ቀጣይ ፈተና አይገጥማቸውም ማለት አይደለም። ኢህአዴግ ያከሸፈውን የፖለቲካ ሴራና የመስመር ዝንፈት መንስኤ እንደገና በጥልቀት በማየት ፍቱን መድሃኒት እንዳበጀለት ማረጋገጥ ይኖርበታል። ህዝቡ ኢህአዴግን ራሱን ለማጥራትና የህዝቡን ፍላጎቶች ለማርካት ደረጃ በደረጃ በትኩረት በመወሰን እየወሰደ ያለውን ርምጃ በበቂ መጠን ተገንዝቦት አብሮት ሊሰራ ዝግጁ መሆኑንን በእርካታው እያረጋገጠለት ስለሆነም ይህን እድል በፍጥነት መጠቀም ይኖርበታል።

ድርጅቱ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የ17 ቀናት ግምገማ ራሱን በመሰረታዊነት ካየና ከፈተሸ በኋላ ሊተገብራቸው ያስቀመጣቸው ዝርዝር ጉዳዮች በታቀዱት መልኩ እንዴት እየሄዱ እንደሆነ፣ ምን ውጤት እንደታየ፣ የህዝቡ አስተያየት ምን እንደሆነ በመዳሰስ እቅዱ እየተፈፀመ ስለመሆኑ በጊዜ የለኝም መንፈስ መከታተል ይኖርበታል። ጉድለት አለባቸው ብሎ የለያቸው፣ የልማት፣ የዴሞክራሲ ማስፋት፣ የመልካም አስተዳደር ማስፈን፣ የአገልገሎት አሰጣጥ ወዘተ ጉዳዮች ከእቅድ ባለፈ ፈፃሚያቸውና አመራራቸው

ሊተገብር የሚያስችል አቅምና የፖለቲካ ዝግጁነት አለው ወይ ብሎም መፈተሽና ርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

ስልጣንን የግል መኖሪያ የማድረግ ችግር በድርጅቱ እንደተስተዋለ የገመገመው ኢህአዴግ የስልጣን አተያይን ህዝባዊነት ለማረጋገጥ የድርጅቱ ሊቀመንበር የወሰዱትን ቁርጠኝነት የተሞላበት ርምጃና ነባራዊ ባህል በጥልቅ ግምገማ ማውረድ ይኖርበታል። በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ህዝብን ለምሬት የሚዳርጉ አሰራሮች ዳግም እንዳይከሰቱ፣ መቀመጫ ማገልገያ እንጂ መገልገያ አለመሆኑን የሚያረጋግጡ ውሳኔዎች በተጨባጭ ማሳየት ይኖርበታል።

ከምንም በላይ የአገሪቱን ህዝቦች ዘላቂ ተጠቃሚነትና የአገሪቱን ቀጣይ የብልፅግና ጉዞ ለማረጋገጥ ብሄራዊ ጥቅምን ያማከለ የትኛውንም ርምጃ በመውሰድ በህዝብና በአገር እንደማይደራደር ያሳየው ኢህአዴግ፣ ችግሮቹን ለመፍታት በተጓዘባቸው ሂደቶች ያጋጠሙ ወጣገባዎች ላይ ሳይሆን በሂደቱ በተገኙ ውጤቶችና ቀጣይነታቸውን በማረጋገጥ ጉዳይ ላይ አቋም በመያዝ ይበልጥ አንድ ሆኖ መገኘት ያለበትም አሁን ነው።

ኢህአዴግ ከህዝቡ በተለያየ መንገድ እየተገለፀለት ያለውን ምስጋናና ለለውጡ አብረን እንሰራለን የሚሉ ዝግጁነቶች፣ አሁንም ለህዝቡ በግልፅነት እያከናወናቸው ያሉ ስራዎችን በማስተዋወቅና የደረሱበትን ውጤት በመግለፅ ትስስሩን ማጥበቅ ይኖርበታል። ከድርጅቱ የረጅም ጊዜ ግብ ስኬት አንፃር ፈተናውን ለማለፍ ያደረገው ጥረት ወሳኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በተለያዩ ምክንያቶች የተጓተቱ የከፍታ ጉዞ ስራዎች በእልህና በቁጭት ተፈፃሚ እየሆኑ ወደ ውጤት እንዲያመሩም አንድነቱን አጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል።

ይህን እውን ለማድረግ ግን በስራ አስፈፃሚውና በማዕከላዊ ኮሚቴ ደረጃ ሲያደርገው የነበረውን ፍተሻ ታች ድረስ በፍጥነት ማውረድ፣ ማስተካከያ ማበጀትና በተመረጠበት ፕሮግራም እንደ መንግስት ለህዝቡ አሳካቸዋለሁ ብሎ ቃል የገባባቸውን ስራዎች በቀሪዎቹ ጊዜያት ህዝብን በሚያረካ አግባብ መጀመሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል።